ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Civil Service Commission

ቁጥር/Ref.No. ፌሲሰ30/ጠ5/736/15

ቀን/Date ግንቦት 29 2015

በዝርዝሩ ለተመለከቱት የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች የጋራ ቅጥርና አስተዳደር መመሪያ 965/2015</u>

<u>ስለመላክ</u>

የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ኮሚሽኑ መመሪያ እንደሚያወጣ በተደነገገው መሠረት ረቂቅ መመሪያው ተዘጋጅቶ ለሁሉም የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤቶች በመላክ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት በኮሚሽኑ የሥራ አመራር ኮሚቴ ጸድቆ ለፍትህ ሚኒስቴር የተላከና መመሪያ ቁጥር 965/2015 በሚል ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ድረ-ገፅ የተጫነ መሆኑን ግንቦት 18 ቀን 2015 ዓ.ም አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች የጋራ ቅጥርና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 965/2015 7 ገፅ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በየመስሪያ ቤቶቻችሁ ተግባራዊ ማድረግ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፣</u>

ለክብርት ም/ኮሚሽነር ጽ/ቤት
ለክቡር ም/ኮሚሽነር ጽ/ቤት
ለኮሚሽነር ጽ/ቤት
ለኢንስፔክሽን ዴስክ ኃላፊ
ለስምሪት ዴስክ ኃላፊ
ለሰው ሀብት ህጎች ዴስክ ኃላፊ
<u>ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን</u>

ስልክ/Tel +251-11-554 96 66 ፋክስ/Fax +251 11 554 97 07 ኢሜል/Email - ethiocs@gmail.com
+251-11-554 96 67 T.ሳ.ቁ./po.box - 1082 ዌብ ሳይት/website - www.csc.gov.et
አዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ከፍላሚንጎ ሬስቶራንት 100 ሜትር ገባ ብሎ
ማገልገል ክብር ነው!

ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Civil Service Commission

# የመንግሥት ሠራተኞች የጋራ ቅጥርና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 965/2015

ግንቦት 10/2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## <u>መመሪያ ቁጥር 965/2015</u>
## <u>የመንግስት ሰራተኞች የጋራ ቅጥርና አስተዳደር መመሪያ</u>

የመንግስት መ/ቤቶች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ በጋራ ቅጥር ለማገልገል ፍላጎት ያላቸውን ሠራተኞች ለማሰማራት በተለይም ባላቸው ልዩ እውቀትና ክህሎት በማስተማር ወይም በምርምር ስራቸው አርአያነት ባለው፣ በግል ሰብእናቸው የታወቁ፣ የስራ ተሞክሮ፣ እውቀት እና የስራ ልምዳቸውን በማካፈል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል፣

በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ በተመዘነና በተፈቀደ ወይም በሙያ እድገት መሰላል ስራ መደብ ላይ ሠራተኛን በጋራ ለመቅጠርና ለማስተዳደር የሚያስችል ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ስርአት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ (2) እና አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ (2) በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የጋራ ቅጥርና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 965/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "**አዋጅ**" ማለት የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ነው፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
3. "**ደንብ**" ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 502/2014 ነው፡፡
4. "**ኮሚሽን**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የተቋቋመው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡
5. "**የስራ መሪ**" ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሥራ ሂደትን በበላይነት የሚመራ ሀላፊ ነው፡፡
6. "**የጋራ ቅጥር ሰራተኛ**" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ባለው ልዩ እውቀትና ክህሎት ተቀጥሮ ይሰራ የነበረ በተጨማሪ በሌላ መ/ቤት የማማከር ወይም ማስተማር ወይም የመሳሰሉት ስራዎችን ተፈቅዶለት በመንግስት ስራ ሰአት እና ቀናት የሚያከናውን ሰራተኛ ነው፡፡
7. "**የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት**" ማለት እውቀት፣ ክህሎት እና ችሎታውን በስራ ላይ በማዋል የተሰጠ ተግባርና ሀላፊነትን በውጤታማነት ማጠናቀቁን ለማረጋገጥ የተሰጠ ማስረጃ ነው፡፡
8. "**ልዩ እውቀት እና ክህሎት**" ማለት ከመደበኛ ትምህርት፣ ስልጠና፣ ተሞክሮ ወይም ስራ ልምድ የተገኘ መረጃን ጥቅም ላይ በማዋል የስራ ውጤት ማስገኘት እና በተከታታይ የመፈጸም ብቃት ነው፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ላይ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

በፌደራል መንግስት በተመደበ በጀት የሚተዳደሩ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና የመንግስት ሰራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. የመመሪያው ዓላማ

1. ከፍተኛ የስራ ልምድ፣ እውቀት የሚጠይቅ እና በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ በተመዘነና በተፈቀደ ወይም በሙያ እድገት መሰላል ስራ መደብ ላይ በመመደብ፣ ልዩ እውቀትና ክህሎት ያላቸውን ሙያተኞች በጋራ በመጠቀም ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ፣

2. ልዩ እውቀትና ክህሎት፣ ብቃትና ስነምግባር የተላበሱ፣ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ እውቀትና ዲጂታል ሲስተም፣ ሀብት ማፈላለግና ማንቀሳቀስ አሠራርን ለሚዘረጉ ሠራተኞች፣

የስራ ስምሪት ለመስጠት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የጋራ ቅጥር አፈጻጸምና አሰራር ስርአት

6. የጋራ ቅጥር የአፈፃፀም ስርአት

1. ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የጋራ ቅጥር ሰራተኛን በመቅጠር መመደብ የሚችለው የትምህርት ደረጃ ሁለተኛ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ በሚጠይቅ በተመዘነና በተፈቀደ ወይም በሙያ እድገት መሰላል የስራ መደብ ላይ ብቻ ነው፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ክፍት የሥራ መደብ ላይ በጋራ ሰራተኛነት ለመቀጠር የሚፈልግ ማንኛውም ሰራተኛ ለስራ መደቡ የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ፣ አይነት እና ቀጥታ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀጠረው ሰራተኛ ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ደረጃ ያለው ከሆነ



መቅሰፍ ኃይሉ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

የሚቀጠርበትን ስራ መደብ ቀጥታ አግባብነት ያለው ስራ በመስራት በተግባር ያሳየ እና ለዚህም ማረጋገጫ ማስረጃ ወይም የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡

4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀጠረው ሰራተኛ የስራ መደቡ የሚጠይቀውን ቀጥታ አግባብነት ያለው ሁለተኛ ዲግሪ ወይም ሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት ደረጃ ያለው ከሆነ የሚቀጠርበት ስራ መደብ ቀጥታ አግባብነት ያለው ስራ በመስራት በተግባር ያሳየ እና መምህር ሆኖ 5 አመት ያስተማረ ወይም በምርምር ስራ ያሳተመ ወይም ፓተንት ያስመዘገበ መሆኑን ማስረጃ ወይም የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡
5. ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የጋራ ቅጥር ሰራተኛው የሚያቀርበውን ማስረጃ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) እስከ (5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ ሰራተኛን ቅጥር የሚፈጸመው የመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ የሰራተኛ ምልመላ በማድረግ በሚሰጠው ውሳኔ እና ሰራተኛው በሚሰጠው ፍቃደኝነት ብቻ ይሆናል፡፡
7. በዚህ መመሪያ መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቱ ማስታወቂያ በማውጣት የጋራ ቅጥር መፈጸም ይችላል፡፡
8. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት በዚህ መመሪያ መሰረት የጋራ ቅጥር ሰራተኛውን ትምህርት ዝግጅት፣ ስራ ልምድ እና የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ማስረጃዎች በማያያዝ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ማሳወቅ አለበት፡፡

## 7. መደበኛ የመንግስት ስራ ሰአት እና ቀናት አጠቃቀም

1. የጋራ ቅጥር ሰራተኛ ከሳምንት የመንግስት ስራ ሰዓት እና ቀናት ውስጥ 80 በመቶ ሳያንስ በተቀጠረበት የመንግስት መስሪያ ቤት ማገልገል አለበት፡፡
2. የጋራ ቅጥር ሰራተኛ ከሳምንት የመንግስት ስራ ሰዓት እና ቀናት ውስጥ እስከ 20 በመቶ ሳይበልጥ በማስተማር ወይም ማማከር ወይም የመሳሰሉትን ስራዎችን ለመስራት ከፈለገ ከሌላ መስሪያ ቤት ጋር የተዋዋለበትን የስራ ውል ስምምነት ሲያቀርብ እንዲሰራ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

3. የጋራ ቅጥር ሰራተኛ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ (2) በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት መቀጠሩን ለቀድሞ ቀጣሪ መስሪያ ቤት ማሳወቅ እና ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡

8. **የጋራ ቅጥር ሠራተኛ ደመወዝ፣ መብት እና ጥቅማ ጥቅም አጠባበቅ**

1. የጋራ ቅጥር ሰራተኛ ደመወዝ ሰራተኛው በተቀጠረበት የስራ መደብ እና ደረጃ መነሻ ደመወዝ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ ቅጥር ሰራተኛ የትምህርት ዝግጅት ሁለተኛ ዲግሪ ከሆነ የሚመደብበት ስራ መደብ እና ደረጃ ከመነሻ ደመወዝ እስከ ሶስት እርከን ድረስ ገባ በማለት ሶስተኛ ዲግሪ ከሆነ ደግሞ ከመነሻ ደመወዝ እስከ አምስት እርከን ድረስ ገባ ብሎ እንዲከፈል የመንግስት መስሪያ ቤቱ መወሰን ይችላል፡፡
3. የዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመደበኛ የመንግስት ስራ ሰዓት እና ቀናት ውስጥ በሳምንት 20 በመቶ ሳይበልጥ በሌላ መ/ቤት የማማከር ወይም ማስተማር ወይም የመሳሰሉ ስራዎችን የሚያከናውን የጋራ ቅጥር ሠራተኛ ከደመወዝ ክፍያ በስተቀር በመንግስት የተፈቀዱ ክፍያ ስርአቶች ተከፋይ መሆን አለበት፡፡
4. የጋራ ቅጥር ሠራተኛ የተመደበበት የስራ መሪ ስራ መደብ ላይ ከሆነ በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ለስራ መሪዎች የተፈቀደው ጥቅማ ጥቅም እና ክፍያ ዓይነቶችን የማግኘት መብት አለው፡፡
5. የጋራ ቅጥሩ ሰራተኛው ቀድሞ በነበረበት መስሪያ ቤት የሚያገኘው ጥቅማ ጥቅም የተሻለ ከሆነ፣ ያልተጠቀመባቸው አመት እረፍት እና የመሳሰሉት ጥቅማ ጥቅሞች ካሉ በጋራ ቀጣሪ አዲሱ መ/ቤት አሰራር ስርአት መሰረት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡
6. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት የጋራ ቅጥር ሠራተኛው ጋር ውል ስምምነት በመፈራረም መኖሪያ ቤት ከመንግስት ተቋም በኪራይ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡
7. የጋራ ቅጥር ሠራተኛ በመስክ እና ከመደበኛ ስራ ቦታ ውጭ ለሚያከናውነው ስራ ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች በመመሪያ የተደነገገውን የአበል ክፍያ እና የትራንስፖርት አገልግሎት ወይም ክፍያ የማግኘት መብት አለው፡፡

9. **አገልግሎት ማቋረጥ እና ወደ ቀድሞ መስሪያ ቤት ስራ ስለመመለስ**

1. የጋራ ቅጥር ሠራተኛ በስድስት ወር የስራ አፈጻጸም ምዘና ከመካከለኛ ውጤት በታች ካገኘ በአፈጻጸም ደረጃ ምክንያት ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ከአዲሱ የጋራ ቀጣሪ መ/ቤት ስራ ይሰናበታል፡፡
2. የጋራ ቅጥር ሠራተኛ የተቀጠረበት የተወሰነ ጊዜ ስራ መጠናቀቁን ወይም በጋራ ቀጣሪ መ/ቤት አገልግሎት ለመስጠት የተስማማበት ስራ በበቂ ሁኔታ መፈፀሙን የመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ አረጋግጦ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ሰራተኛው ወደ ቀድሞ ቀጣሪ መ/ቤቱ ስራ ይመለሳል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. **የተከለከሉ ተግባራት**

የዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም መንግስት መስሪያ ቤት በተመዘነና በተፈቀደ ወይም በሙያ እድገት መሰላል ስራ መደብ ብዛት ሁለት ከመቶ (2%) በላይ የጋራ ቅጥር መፈጸም የለበትም፡፡

11. **ሌሎች ህጎችን ተፈጻሚ ስለማድረግ**

1. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በስራ ላይ ባለው የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንቦች እና መመሪያዎች ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች የሠራተኛው የጋራ ቅጥር ሁኔታዎች፣ የስራ ስምሪቶች፣ የስራ ሁኔታ፣ የሠራተኛው መብት እና ግዴታዎች ጥቅምት 5 ቀን 2011 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች የምልመላና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፡፡
3. የሌሎች ህጎች ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሠራተኛን በጋራ ስለመቅጠር የመንግስት መ/ቤቶች ስምምነት መፈጸም ይችላሉ፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

12. **ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ህጎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

13. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ኮሚሽኑ በማንኛውም ጊዜ ይህን መመሪያ እና የመመሪያውን አንቀጾች ማሻሻል ይቻላል፡፡

14. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ዶ/ር)
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
ኮሚሽነር

**ለግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
- የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
- የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን
- የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
- የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት
- የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ ደን ልማት
- የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት

**ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

**ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት
- የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን

**ለማዕድን ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት
- የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

**ለቱሪዝም ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን
- የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን

**ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት
- የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
- የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
- የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
- የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
- ሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
- የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
- የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ኢንስቲትዩት

**ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ
- የመንግስት ግዢ አገልግሎት
- የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር

**ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት
- የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት
- የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

**ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን
- የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

**ለትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን
- የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን
- የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት

**ለከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት
- የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን

**ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት
- የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት
- የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

**ለመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስቴር**

**ለትምህርት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ
- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ

- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
- የወለጋ ዩኒቨርሲቲ
- የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
- የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ
- የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ
- የመቐሌ ዩኒቨርሲቲ
- የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
- የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ
- የአክሱም ዩኒቨርስቲ
- የሰመራ ዩኒቨርስቲ
- የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
- የአምቦ ዩኒቨርሲቲ
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ
- የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ
- የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ
- የዲላ ዩኒቨርሲቲ
- የጎንደር ዩኒቨርሲቲ
- የሃዋሣ ዩኒቨርሲቲ
- የወሎ ዩኒቨርሲቲ
- የመቱ ዩኒቨርሲቲ
- የአዲግራት ዩኒቨርሲቲ
- የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ
- የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ
- የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ
- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨር1ሲቲ
- የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ
- የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ
- የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ
- የጋምቤላ ዩኒቨርስቲ
- የአርሲ ዩኒቨርስቲ
- የዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ
- የወራቤ ዩኒቨርስቲ
- የቦንጋ ዩኒቨርስቲ
- የመቅደላ ዩኒቨርስቲ
- የደባርቅ ዩኒቨርስቲ
- የደንቢዶሎ ዩኒቨርስቲ
- የእንጅባራ ዩኒቨርስቲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

- የአዳቡልቱም ዩኒቨርስቲ
- የሰላሌ ዩኒቨርስቲ
- የራያ ዩኒቨርስቲ
- የጂንካ ዩኒቨርስቲ
- የቀብሪደሀር ዩኒቨርስቲ
- የቦረና ዩኒቨርስቲ
- የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ
- የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርስቲ
- የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት
- የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን

**ለጤና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት
- የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ ጤና መድን አስተዳደር
- የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ድርጅት
- የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን
- ቅዱስ ጴጥሮስ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
- ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ
- አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
- የአለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
- የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት
- የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል

**ለሴቶች ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር**

**ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ ዲያስፓራ አገልግሎት

**ለፍትህ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን
- የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን
- የፌደራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት
- የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ  አገልግሎት
- የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ

**ለሰላም ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋም**

- ሀገራዊ የምክክር መድረክ ኮሚሽን

**ለባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ
- የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን
- የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር

**ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት እና ተጠሪ ተቋማት**

- የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
- የቤተ-መንግሥት አስተዳደር
- የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን
- የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ
- የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን
- የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
- የፌዴራል ሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን
- የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት
- የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት
- የብሔራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን
- የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት

**ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**

**ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴሬሽን ምክር ቤት**